በገበያ ሲሸጥ የፍሬዬ ሰብል
አልፎ ሃጁን ሁሉ ያነሆልላል ።
ከብቴን አረባለሁ በቈላ ቈላው
ወተትና ሥጋ ልጄ እንዳያምረው ።
ያለኝን በጭሩ ይኸው ነገርሁህ
ደግሞም ከዚህ ሌላ ምነው ጥያቄህ ።

ል ብ     ስላጨዋወትሽኝ ተመስገኝ እናቴ
መወድስ ሰጥቼሽ ልሂድ ወድቤቴ

መ ወ ድ ስ ።

ምድረ ኤርትራ ጆሮሽ ከሩቅ የሚሰማ
ሲገረፍ ሰምቶ ጥበብ የምዕራብ ጅራፍ ዛሬ
አዘዘው በጥብቅ የዘመኑን ዕውቀት መረሬ
እንዳያርሰው በቀና ልቡና ልጅሽ ገበሬ
እሱም ትእዛዝሽን ሰምቶ
ይነዳው ጀመር በኃይል የምዕራብን ስልት በሬ
ጆሮሽሂ ምድረ ኤርትራ የዓለም ሥልጣኔን ወሬ
ሰምቶ ያሳየዋል ለብሩህ ዐይንሽ ምድረ ትግሬ
ድንገት ቢጥለኝ እኔም አንክሮ ጥበባት እግሬ
ተመለስሁ በማለዳ የጆሮሽን ጌጥ ሳደንቅ አድሬ ።

ምዕራፍ ፳ ጐጃም (አንደበት)

መ ግ ለ ጫ ።

በማርና በወተት በእህልና በከብት ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ሁሉ ይበልጣል ተብሎ የሚገመተው ጐጃም ነው ። ዛፉም ፡ ሣሩም ፡ ወንዛም ፡ ዱሩም ነው ፤ በጋ የሚ ደርቅ ወንዝ የለበትም ሜዳውና ተራራው ዘለዓለም ልምላሜ አይለየውም ፤ ኮንካ መ ሬት የለበትም ። ከከፋ ፡ ከወለጋ ከኢሉባቦር ደኖች የሚወዳደሩ ጫካዎች በጉታና በመተከል ይገኛሉ ። ማሩ ዘይንትረፍ ወተቱና ቅቤው ዝልኪ ምልኪ ነው ፤ ያብዛኛው ሕዝብ ኑሮ በግብርና ነው ። ሰው በተፈጥሮው ዐዋቂና ጀግና ሩኅሩኅና ለጋስ ነው ። ሀገርዋ የመጻሕፍት መፈታቻ የቅኔ መፈጠሪያ ናት ።

ካህን ፡ ጨዋ ፡ መኰንን ፡ ወይዘሮ ፡ ከተሜ ፡ ባላገር ፡ ጌታ ፡ ሎሌ ፡ ሳይለይ በመላ ሕዝቡ የሚነጋገረው በቅኔ ስለሆነ ከደምበር ከተቀመጡት ሽማግሎች አንሥቶ ከበረት ላም እስከሚያራክቡት እረኞች ድረስ የሚጫወቱበት የንግግር ስልት ኀብር ፡ ውስጠ ወይራ ፡ ሰም ለበስ ወዘተ ነው ልቅሶና ዘፈኑም ቅኔ ነው ፡ አንደበትም የተባለበት ዋና

ው ዓላማ ይህ ነው ። በመላ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ፈሪ ፡ ሰንበትን አክባሪ ፡ ጾም ጸዋሚ ነው ። ሴቱም ወንዱም ርኅሩኅ ስለሆነ ቀን ሲርበው ወደ መንደር ጐራ እያለ ፡ ሲመሽ በት የእግዜር እንግዳ ብሎ እያደረ ይጓዛል እንጅ ማነኛቸውም መንገደኛ ስንቅ አይፈ ልግም ። ተማሪም ለምግቡ ምንም ሳያስብ ለምኖ እየበላ ትምህርቱን ሲጨርስ ወደ ሀገ ሩ ይመለሳል ። ሊቃውንቱ በጐጃም የሚበዙበት ምክንያትም ሀገሩ ጥጋብ ሰው ሩኅ ሩኅ ስለሆነ ነው ። በዘመናዊ አጠራር ዩኒበርስቲ ሊባሉ የሚችሉት የቅኔ ምስክሮች ዋሸራና ጐንጅ የመጽሐፍ ሞጣና ቀራንዮ ፡ ዲማ ደብረ ወርቅ የሚገኙት ከዚህ ነው ።

መሬቱ የሰጡትን ሁሉ ያላንዳች አረም ያበቅላል ፤ በጐጃም የማይገኝ አንድ ጨው ብቻ ነበር እሱም ከስድስት ዓመት ወዲህ ካራት ላይ መገኘቱ ተረጋግጧል ።

ዋና ከተማው ደብረ ማርቆስ ነው ።

ዓሣ ያላቸው ወንዞች ፤

ዐባይ ፡ አበያ ፡ የዳ ፡ ጀማ ፡ ዳቦላ ፡ ክልቲ ፡ በለስ ፡ ላህ ፡ ፈጣም ፡ ዱራ ፡ ተምጫ ፡ ብር፡ ሌሎች ታናናሾችም አሉ ።

ብዙ ደሴቶች የያዘው ሐይቅ ጣና ነው ።

አውራጃዎች ፤ ሀ) ደብረ ማርቆስ ፡ ለ) ብቸና ፡ ሐ) ደጋ ዳሞት ፡ መ) ሞጣ ሠ) ቡሬ ዳሞት ፡ ረ) ባሕር ዳር ፤ ሰ) አገው ምድር ደንግላ ቀ) መተከል ቀዳማዊ በር ናቸው ።

ወሰን ፡ በሰሜን ከበጌምድር በምዕራብ ከሱዳን ፡ በደቡብ ከወለጋና ፡ ከሸዋ ፡ በም ሥራቅ ከወሎና ከሸዋ ይዋሰናል ።

መጣጣ አይብ ፡ ጉዝጉዝ ምጣድ ሽሮ ፡ ወተት ሽሮ ፡ ቁብታ በሌላ ሀገር የሌሉ የጐ ጃም ምግቦች አሉ ። በእየበረሃው ዕጣን ሞልቷል ። ከሱዳንና ከወለጋ አዋሳኝ ብዙ የበረኻ አራዊት ይገኛሉ ወርቅም በወምበራ ሞልቷል ። ቡን በቡሬ በመተከል በዘጌ ይበቅላል ። ብዙ መዋቶች አሉ ።

ልብ            እንደበትሽ ጐጃም ምታወሪበት
ሲያዘንም ይኖራል ማርና ወተት
ቢውጡት ቢውጡት የማይሰለቸው
ቅመም ያጣፈጠው ቅቤና ማር ነው
ወሬሽ ሰምና ወርቅ ወግሽ ሰም ለበስ
ቅኔሽም ኅብር ነው አንጀት የሚያርስ
ቲያትር ሲኒማ ዘመን ያመጣው
ውድድር ጭዋታ ሰው የሚወደው
ይህ ሁሉ ቀርቶብኝ በበዓል በዕረፍቴ
ልቡናዬ ይርካ ይራስ አካላቴ
ጉልበቴ ይጠንክር ይለምልም አጥንቴ
ከቅኔሽ አቅምሽኝ እባክሽ እናቴ ።
ለይታ ካወቀች ጽድቅና ኵነኔ

በጣም ያስደንቃል የሴት ባለቅኔ ።
ቅኔ ለማስተማር ጉባኤ ዘርግተሽ
ሐዲስና ብሉይ ሁሉን ፈትተሽ
ሊቃውንት አዋልድ አንድም ሳይቀርሽ
በዚህ እንደበትሽ ታስተምሪአለሽ
ዕውቀትሽን የሰማ ዓለም ገረመው
ቢያጠናው ቢማረው መቼ ዘለቀው
ከዚህ ሁሉም በላይ ወግሽ ይጣፍጣል
ካንደበት ሲወጣ ሰሚው ይገረማል
በጣም የሚደመኝ ስታወሪ ወሬ
ከቤት እንስሳና ደግሞም ከዱር አውሬ
ይደንቀኝ ነበረ ትላንት ስሰማው
ሁሉንም በተራ ስትተነትኚው
ያለሽን ሀብት ሁሉ በተራ ንገሪኝ
እባክሽ እማዬ መጠኑ ቸገረኝ

**ኢትዮጵያ** ለጊዜው በአንደበት እኔ ምነግርህ
በጣም ትንሽ ናቸው ብዙ አይምሰሉህ
መታገሥ አለብህ ሁሉን እንድታይ
ታቅፌ እስካሳይህ ከደረቴ ላይ
በእጄም የያዝሁትን ያቆምሁትን በግሬ
አሳይሃለሁኝ አትቸኩል ለወሬ
ለጊዜው ትዝ ሚለኝ የያዝሁት ንብረት
ከውጭ ከሜዳ ደግሞውንም ከቤት
ማጀት በጐረሰ ደጃፍ በመለሰ
የሚከተለው ነው ልቤም አስታወሰ
በሬውና ላሙ በጉና ፍየሉ
በቅሎና ፍረሱ ሁሉም በበኩሉ
ጊደሩ ወይፈኑ ወገዙና ከብቱ
ጥጃውና እንቦሳው የቤት እንስሳቱ
በጣም ያስደስታል ላየ ሲጫወቱ
ቅዱሱን ለመብል ርኩስ ለጭነት
ይኸው አረባለሁ ለሰው ልጅ ሕይወት
ደረቤና እኑብሴ ሞጣ እንዘ ግድም
የከብት ሽኃዬ ነው እስከ ላይ ጐጃም
በመላ አገው ምድር ደጋ ዳሞት ሁሉ

ጨፌውን የበሉ ሽልቦች ቡ ይላሉ ።
ከዕለታት አንድ ቀን ታሪክ ተሠራልህ
አሁን ትዝ እንዳለኝ ሳልረሳው ልንገርህ
አገው ምድር ሁኖ በሬዬ ቢያገሳ
ተሽብሮ አደረ ይልማናና ዴንሳ
አቸፈር ወንድጌ አለፋ ጣቁሳ
ልጃንበራ ጉታስ ዕቃም አላነሳ
ሜጫና ቆለላ በመላ ዳሞት
ሲጨነቅ አደረ ነገሩ ጠፍቶት
ሞጣ ቀራንዮ ጐጃም ተሸበረ
ልቡን ያልጨነቀው አንድም አልነበረ
ከብት አለኝ ወርቅ አለኝ እህልም እንደ ልብ
ለሰው አቀናለሁ እንኳን እኔ እራብ
ብታየው ገንዳዬን አገው ምድርን
ቀፎ መስቀያዬን ቡሬ ዳሞትን
መተከል ጓሮዬን ጫራ ተጋኜን
ገነተ ተድላነሽ ትል ነበር ባማን ።
ወተት ከበረቴ ማሩን ከገንዳዬ
ሁል ጊዜ አገኛለሁ እንደ ልቡናዬ
ማር እንደ ጭቃ ነው ቅቤም እንደ እበት
የምቈጥረው እኔ ባገው በዳሞት
እኔን ሚቸግረኝ አንድ ጨው ነበረ
እሱንም አገኘሁ እሰይ ችግር ቀረ (ሊበንና ጅበላ)
መጣጣና ቅቤ አይብና ወተት
አጓት ዝንቡድባጅ ወፍራም ወገሚት
እንገራ ምናሁሬ እርጎ ስልባቦት
ሁሉም ይጣፍጣል ጨው ካለ ከቤት
ማሬ የለው ከዳ ደግሞ አንዳች ሰፈፍ
ከወለላ በቀር መቸም የለው እድፍ
ዓለም አደነቀው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ
የጣዝማ ማር አለኝ በትክሲ (ምልጭ) ሚገኝ
የልጆቼን አምሮት እሱው ቻለልኝ
ዲን እንኳ የለውም እንደ ሌሎች ሀገር
ዘፍና ሰፈፍም ከወለላ በቀር
ወተት እንደ ልብ ነው ከቤቴ ማገባ

ላሜ ትሰጣለች ጥኂት አምስት ቦልባ
ወተቱን ባየኸኝ ሳንደለዱለው
ወዲህ በግራራው ወዲህ በዲሎው
ማሦርና ቋጫ ቅሌ ሁሉ ሞልቶ
ጥጃው ፈረጠጠ የቀረውን ጠብቶ ።
ከበረቴ መጥተህ ግብሬን በየኸው
ማሦሮው ሲሞላ ሲጐርፍ አረፋው
ሰዎች ተሰብስበው ውጤት ለማየት
ሳሙናና ወፍጨጭ ሁሉም አንድነት
የወተቱ አረፋ በልጦ ቢታያቸው
አእምሯቸው ሰክሮ ተማርኮ ልባቸው ።
እያጨበጨቡ ሲያመስግኑኝ
ይገርምህ ነበረ አንተም ብትገኝ

ልብ — ወለላሽን ውጠሽ ወተት ጠጥተሽ
አልቦሽ ወረደ ዐባዩ ወዝሽ
ይህን ዐባይ ወዝሽን በመሐረም ጠርጋ
ግብጽ ትጠጣዋለች ክረምትና በጋ ።
አንቺ ስቴሆኝ በጣም ባለለዛ
ምነው እነስናር እንዲህ አጡ ሙዛ ።
የላብሽን ብዛት ወንዝ ነው አሉኝ
እረ ከምን ይሆን ይህ ሁሉ ሚገኝ ።
ጭዋታሽ ሦከሩ ማር ንግግርሽ
ዓለሙን ማረከው ሁሉም ሞተልሽ
እኔ ሀብትሽ ብዬ ሰውን የሳበው
ለካስ አንደበትሽ ዓለሙን ፈጀው ።
ወንዞችሽ በሞላ ጤናማ ናቸው (ጥቂር ውኃ ገራይ)
ለሚጠጣቸው ሁል የዚህ ዓለም ሰው
መቸም ያኖሩሻል በዓለም አኵርተው ።
እኔም ትንሽ ወሬ ከሰው ሰማሁኝ
ከሁሉ የሚበልጥ ዐባይ ነው አሉኝ
እናት እንመለስ ወደ አርእስታችን
ደግሞም ከእህል ወገን ንገሪኝ ሁሉን ።

ኢትዮጵያ — ስለ እህል ዐይነቶች እኔ ባወጋህ
አትሰማኝም አንተ ትሰለቻለህ ።

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

**ልብ** እናቴ አውሪኝ እንጂ እኔስ አልሰለችም
አንደበትሽ ማር ነው አይጠገብ መችም

**ኢትዮጵያ** ምትሰማኝ ከሆነ ለጥቅም ብለህ
በላ ተቀበበኝ ጆሮህን ከፍተህ ።
ጤፍና ስንዴ ነው ዋናው አዝመራዬ
ተዘርቶ ሚታየው በሰፊው ሜዳዬ ።
ጤፍ ብዙ ዐይነት አለው ለቊጥር ሚያስቸግር
ደግሞም ስንዴ እንዲሁ ልብ የሚያደናግር
ገብስና ዳጉሳ መልካም ጠላቸው
በጣም ይጣፍጣል ለቀመሳቸው ።
ገብስ ብዙ ዐይነት አለው እንዲሁም ዳጉሳ
በጽሕፈት ካልሆነ በቃል ማይወሳ
ሰመሬታ ጠበል ወለምና መስኖ
ሰውን ያስጐመጃል ሲታይ ተኰፍኖ ።
ሰነፍ ቄሎና አጃ እንዲሁም ጠመጅ
ከማሳዬ ሲታይ ሰውን ሚያስጐመጅ ።
ያበቅላል ማሳዬ ያላንዳች አረም
በሮቼ ሳሉልኝ ሚቸግር የለም ።
ጉብሴን ዘራሁት ተልባና ኑግን
ሁራዬን ማሽላ (በቆሎ) ግብጦ ጤፍ ቀድሜን
ሙዝዬና ድንች ጐመን ተጋኔን
በሞላ መሬቴን ልዩ ልዩ አትክልት
ልጆቼን በሰላም ማሳድግበት
ሁል ጊዜ አቀናለሁ መቸም አልሸምት
ይህን የሚያስረዳ አለልኝ ተረት
ምን ራብ ቢጠና ጐጃም በሙት ሙቱ
ይሻላል ልጆቼ ሂደችሁ ሸምቱ
ምስርና ስንዲ ጓያና ሽንብራ
ስንቱን ልቊጠርልህ ያገሬን አዝመራ
እነግርህ ነበረ ብዙውን እህል
ካሬ ደርሶ ጠፋኝ እኔ ምን ልበል ።

**ልብ** ነገርሽኝ ባጭሩ ስለቤት እንስሳ
ደግሞም ስላዝመራ ሁሉም ባይወሳ ።
አሁንም ሳትሰለች እባክሽ አውሪኝ
ስለዱር አራዊት ትንሽ ንገሪኝ ።

ኢትዮጵያ    በላ ትንሽ ላውራህ እኔ ምን ዕዳዬ
አንተ ለምትሰማው ደስ ካለህ ወሬዬ
በአራዊት መኖሪያ ዐባይ በረሃዬ
በቈላ በደጋው በሰፊው ሜዳዬ
ይገኛሉ አውሬዎች ቍጥራቸው የበዛ
ባንደበት አያልቁም ሁሉም እንደዋዛ
በጽሒፈት ነው እንጂ እያሰላሰሉ
ተዘግቦ የሚያዝ የሚታወስ ሁሉ ።

ልብ    እናቴ ዝም ብለሽ አይዘሽ ተናገሪ
አይባልምና ያለውን ወርዋሪ
በጁ ካላስቀረ መሣሪያውን ፈሪ
ንፉግም አይባል ሰው ሁሉ ምን ቢሆን
ለነገዩ ሳይል ከሰጠ ያለውን

ኢትዮጵያ    ከሙሉ በክፍሉ ዛሬ እነግርሃለሁ
የቀረውን ደግሞ በእጄ አሳይሃለሁ ።
የሚበሉ እንስሳት ፊቆና አጋዘን
ልብ ያስደስታሉ ደግሞም ሕሊናን
ድኩላና ጐማ ሚዳቋና ሰስ
ቡኸርና ሳላ ደግሞም አውራሪስ
በጨረቃ በብር በላህ በፈጣም
እንደ አገው ምድር በግ እንደ አቸፈር ላም
ባየኸው ደፋርሳን አንድነት ሲተም ።
የደረቤን መንጋ የእነማይን ከብት
መስሎ ያስገርማል አሻግሮ ሲያዩት ።
ካራዊትም ደግሞ ጦጣና ዝንጀሮ
ጉሬዛና አሳማ እሪያና ከርከሮ
አፍን ሞጭሞጭላ ተኩላና ቀበሮ
አነርና ነብር ግስላና አንበሳ
ቀጭኔና ዝሆን ታላቆች እንስሳ
በንገዝ የዱር ድመት የቀፎ ጠላት
እሾህ ጦርዋን ታጥቃ ያላንዳች ፍርሃት
ፋሮ በቈፈረው ትገኛለች ጃርት ።
ዥብና ሞቾካይ ደግሞም ማሻንብል
ሌሎችም ብዙ አሉ ተረሣኝ በቃል

ልብ    አራዊት እንስሳን ሰማሁኝ በጭሩ

ስለአዕዋፍ ንገሪኝ ደግሞ እንደነገሩ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ሲሳይ በገፍ ነው ለሁሉ ፍጥረት
ላሞራና ለወፍ ደግሞም ላራዊት
ስለዚህ ልጄ ሆይ እግር ቢጥልህ
ከዕለታት አንድ ቀን ወደዚህ መጠህ
በጣም ታደንቃለህ ሲበሩ ብታይ
ወሰን የሌላቸው ወፎች በሰማይ ።
ዳክዬና ሰረን <u>ገድዬና ይብራ</u>
ጋጋኖና ጭልፊት <u>አመቴና</u> ቍራ ።
ርግብና <u>ቡላል</u> ራዛና ሽመላ
ንስር <u>ግልገል አንሣ ጩሊሊና ሲላ</u>
ታክቦ ይታያል አንድነት ሲበላ ።
ተራራ ብትወጣ ሾላ ልትለቅም
የማማቱ ብዛት ቍጥር የለውም ።

በዕፀዋት በኩልም በጣም ሀብታም ነኝ
የሚወዳደረኝ ማንም አይገኝ ።
<u>ገተም</u> ትልቅ ዕንጨት ዓለም ያወቀው
ንቧ የምትቀሠመው ማር ነው አበበው
<u>እሼ</u> ዋርካ ሾላ ፍሬያቸው ለምለም
ሽምጠ ከበላ ልጅ ምሳ አይልም ።
አጋምና ቀጋ ዋንዛና እንጆርይ
እግዚአብሔር ሰጥቶኛል ለልጄ ሲሳይ ።
ለንቋጣና ዶቅማ በበጋው ሲታይ
ፍሬው የከበደው ይመስላል እንኮይ
ውጋግራዬ <u>ጨባ ሙርሙኝ</u> ምሰሰው
ደገፋዬ ኮማ የከረከረው
የጥዱን ሳንቃዬ ዓለም ያወቀው
ጠንካራ ነው ቤቴ መውደቂያም የለው
ሸንበቆ ቅርቃት ካቶ ቍልቋል ጋራ
ጨፈቃ ጨምረው ይችሉኛል ጣራ ።
አብታና ኮማ ወይራና <u>አዛምራ</u>
ግንዱ ለእሳት ሲሆን ቅጠሉ ለጠላ
ያገለግለኛል ሕይወቴን በሞላ ።
<u>ዶንግና ምሳና ቀላቦና አንፋር</u>

ቃሞ ዱር አባሉ ጨበና ግራር
ሲነድ እሳታቸው እንደምን ያምር ።
ኩሻ ገብረ ጠላ ውልክፋና አውራ
ችለው ይኖራሉ የገመዱን ሥራ ።
ከእነዚህም ሌላ ብዙ ዕፀዋት አሉ
ለሰው ልጅ መድኀኒት ሊሆኑ ሚችሉ ።
ልጆቹ ሲዋኙ ሲሰፉ እንድታይ
በጭር ታጠቅና እንውረድ ዐባይ ።
ዋናተኛው ልጇ የባሕር አምባዛ
ገባ ተመልከተው ዘሎ እንደ ጉሬዛ
የባሕሩ መርከብ የሙላት ባቡር
እያጨበጨበ ወንዙን ሲሻገር
በጥፌ እየመታ ማዕበል ሲያስገብር
በእየወንዙ ወርዶ ዓሣ ሲያሠግር ።
ይመስላል በሩቁ አዞና ጉማሬ
ባሕሩን ሲሠነጥቅ ትልቅ ዓሣ አንበሪ ።

ልብ

ዐየሁት እማዬ ያው እጅ ይጥላል
በኀይል ሲወረወር እባብ ይመስላል ።
በጣሙን ይገርማል ልዩ ነው ዋናው
እጅማ አወጣጡ ጓደኛም የለው ።
ውኃውን ሠንጥቆ እንዲህ የሚበር
ዋናተኛው ልጅሽ የት ነው የሚማር ።

ኢትዮጵያ

ስንቱን ቈጥሬው ነው ለውኃ መዋኛማ
አበያና ፈጣም ዐባይና ጀማ ።
ጨሞጋና ጥምብል አዮና በለስ
ካፋፉ ላይ ብትሆን ይታያል ሲፈስ ።
የዳ ሱኃ ብርም ዱራና በጨት
ዕየው ሲግፈጠፈጥ በበጋ ሙላት
ዓመቱን በሞላ በጋና ክረምት
ልጆቹ ጠንክረው የሚዋኙበት
አለኝ ስመጥሩ ወንዝና ጅረት ።
በእነዚህ ወንዞቼ ብታየኝ ስዋኝ
አዞና ጉማሬ ዓሣ አንብሬ ነኝ ።
ስጠልቅም እንዲሁ አቁስጣና ይብራ
መስዬ እታያለሁ በበለስ በዱራ ።

ዐባይን ቈርጬ ጣናን ብቀደው
ያየኝ ተገረመ ተደነቀ ሰው ።
ዐባይ ከመጣን ጣና ከወረድን
ዋናው ይቈይና ላውጋህ ዓሣውን ።
በመረብ በቅርጫት በብዙ ብርበራ
ተጠምዶ ተይዞ ሁሉም በየተራ
አምሮ ተከሽኖ በጥበብ ሲሠራ
ያስፈራል እጅህን እንኳንስ እንጀራ ።
በወንዞቼ ሁሉ ዓሣው በጣም በዝቶ
ሰው ስለ ጠገበ የሚያሠግር ጠፍቶ
አቁስጣ ጨረሰው ከትክቶ ከትክቶ።
የዐባይ ዳር ለዳሩ የጣና ክበቡ
የታላላቅ ድርጅት የወንዝ አጠገቡ
በመላ ዘመዴ ዓሣ ነው ቀለቡ ።
ድምብክ ገበርማ ዓሣ በቅርጫት
ሲሰፈር ይታያል እንደ ጤፉ ምርት ።
የገበርማ ሰው ሸክሙ ቢደክመው
በፈረስ በበቅሎ ባህያ ጫነው ።
በወንዝ በጅረቱ የሚዛቀውን
ለፍልፌ ላልዘለቀው እባክህ ይብቃን
ደረቁ ጨዋታ እንዳይሰለቹን
ደግሞም እንዲጣፍጥ ማሩ ወጋችን ።
ወጉን ስናወጋ ቡና ላስፈላልህ
ዘኄ ቡሬ ዳሞት መተከል ሳለልህ ።
በወተት ነው በማር ቡና የምትጠጣ
ንገረኝ በቶሎ አንዱን እንዳመጣ ።

**ልብ** እኔ ምን አውቃለሁ ከቤትሽ ያለውን
መቸገሩን ትተሽ አምጪ የተገኘውን ።

**ኢትዮጵያ** ይመስገን ፈጣሪ አሟልቶ ሰጥቶኛል
ዶሮ ወተት በቀር ምን ይጐድልብኛል ።

**ልብ** እንግዲያስ እናቴ በማሩ ይሁንልኝ
ዛሬ ጾም ነውና ወተቱ ይቈየኝ

**ኢትዮጵያ** እሰይ እሰይ ልጄ እንኳም ኖርህልኝ
እጾማለሁ ብትል በጣም ደስ አለኝ ።
ልጄ ብዙ ሰዎች ምግባርን ሲንቁ

ጾምና ጸሎትን በፋቸው ሲያጠቁ ።
ይነደኝ ነበረ እየሰማሁኝ
አሁን ግን ባንተ ላይ ሙሉ ተስፋ አለኝ።
ሃይማኖት አዝመራ ፍሬ ከሌለው
ገለባና ቅጠል ወሬ ብቻ ነው
ባሸሾ ይቀራል ዋግ እንደመታው ።
መጻሕፍትን ማንበብ ትርጉም መተርጐም
ምግባር ከሌለበት ጥቅም የለውም ።
ከሴማው ወጥቼ ወሬ አበዛሁብህ
እባክህን ልጄ አይቀየም ልብህ ።

ልብ — በናው እስኪፈላ ማሩ እስኪነጠር
በዩ አውጊኝ እናቴ ሁሉንም ነገር ።

ኢትዮጵያ — ከፈቀድህልኝስ ብዙ አወጋሃለሁ
ደግሞም ቢያስፈልገኝ እጠይቅሃለሁ
በሕይወቴ ሙሉ እንግዳ እወዳለሁ
ሰንበትን አክብሬ ጾምን እጾማለሁ ።

ልብ — አበሉ እስኪጠጣ ቶናው እስኪደርስ
በረካው ሲፈላ ሁሉ እስኪጨረስ ።
እናቴ እስኪ አቅምሽኝ ከማሩ ቅኔሽ
ደግሞም ከወለላው ፍርንዱስ አርገሽ
ከጠራው ወተትሽ ከሰምና ወርቅ
ከቅቤም ሰም ለበስ ሳልሞት እንድጸድቅ።
ከርጎውም አጠጭኝ የቅኔ ጉዳና
ልጅስ ደስ ይበለኝ ሞት አይቀርምና ።
ድንቍርና ብርዱ እንዳያጠቃኝ
ዘይቤ ኮበርትሽን እባክሽ ስጭኝ ።
ልጅሽን እንዳይበላኝ ሙላቱ ስንፍና
ሰዋስው ጣዩልኝ እናቴ ነዩና ።
ራቁቴን ሁኜ ሰው እንዳይንቀኝ
አደራሽ እናቴ ጥበብ ሥሪልኝ ።
በቅኔሽ ጉዳና ዓለሙን ደርሼ
እመ ተቀበዩኝ መጣሁ ተመልሼ ።

ኢትዮጵያ — ልጄ እንኳን ተመለስህ እንኳን መጣህልኝ
የማወራህ ወሬ ብዙ ነገር አለኝ።

ሰምና ወርቅ ብለህ የጠየቅኸኝን
ይኸው አመጣሁት ተቀበል አሁን ።
ወርቁን ከወምበራ ከሱዳን ጠረፍ
ሰሙን ከገው ምድር ከከዳ ሰፈፍ ።
ቅኔን ከተዋነይ ከታላቁ ሊቅ
ፍላጻን ከጀግኖች ገዝቼ በወርቅ ።
ጥበብ ጥበብ ስትል እኔ እንደ ሰማሁ
ጥጡን ለመመዘን ወደ ቊጭ ወረድሁ ።
ከማዳመጥ በፊት ፍንዱን አሳስቼ
ዳመጠውን ሁሉ ቀኑን አባዝቼ።
ባዘቶን ነድፌ በጀንዲ ቄልዩ
ደግሞ ነጩን ንድፍ እኔው አመልምዬ
ስስበው አደርሁኝ ሌሊቱን ቊጭ ብዬ ።
ከጨረስሁ በኋላ ድርና ማጉን
ሁሉም የቤት ሥራ ሚያስደንቅ ሰውን ።
ሸማኔ ጠርቼ የሊቆችን ሊቅ
እንዲሠራ አዘዝሁት ጥበቡን በጥብቅ ።
ብርድ ልብስ ብርድ ልብስ እመ ብትለኝ
ደጋ ዳሞት ሂጀ በግ አስሸለትሁኝ ።
አቸፈር መተከል ከበረቴ ሂጀ
ወተት ይገፍ መጣሁ እንዳይበርድህ ልጄ ።
ቅቤን ከደረቤ ይዤልህ አንድ አፍታ
ይኸው ከተፍ አልሁኝ ና ብላ ቊብታ ።
እንካ ተቀበለኝ ልጄ ሁሉንም
ከጠየቅኸኝ ሁሉ የቀረ የለም ።

ልብ ዐውቃለሁ እናቴ ባለሙያ ነሽ
በጣም አመሰግንሁ ስለ ስጦታሽ
የቃሉ ኅብርነት ምሥጢሩ ነጥቆሽ
ቅኔ ብጠይቅሽ ገንዘብ አመጣሽ ።
ስላሁኑ ስጦታሽ እጅ እየነሣሁ
ዝነኛው ቅኔሽን ደጅ እጠናለሁ ።

ኢትዮጵያ ቅኔማ ምን ገዶ እኔ ምን ቸገረኝ
አንተን ካልደከመህ በላ ተቀበለኝ ።

ልብ እማዬ ተሰማኝ ከጎረቤት ድምጥ
ቅኔው ይቈይና ነዪ እስኪ እንሩጥ ።

ከጎረቤታችን ደርሷል አንድ እክል
መርዶ ነው መሰለኝ ጩኸት ይሰማል ።
ወሬሽን ሚወዱት ግብጽና ሱዳን
መከራቸው ጠንቶ ቢያዋዩሽ አንችን
ታለቅሽላቸውአለሽ ዐባይ ዐባዩን ።
በአንደበትሽ ገጥመሽ ብታቀነቅኝ
ዐይኔን ውኃ በላው ጣና ሆነብኝ ።
ራምኖን ሙታ ግብጽ ታለቅሳለች
ልምላሜን ተረድታ ሱዳንም ዋይ አለች ።
እመ እንዳንደብትሽ ደግሞ እንደ ቃልሽ
ፍርንዱስ ማዕበልን ባባዩ ጋንሽ
ሰከላ በጥብጠሽ ጣና ላይ ሹመሽ
ይዘሽ ከተፍ በዩ ካዘኑ እባክሽ።
ሰው ሁሉ ይቅመሰው ዝልልሽን ልምላሜ
እኔ ብቻ እንዳልቀር እመ ተገርሜ ።

ኢትዮጵያ
ልጄ ባትለኝም ለመልካሙ ሥራ
ስሮጥ እደርሳለሁ ለሁሉ ስራራ ።
ለመከራ ጊዜ እናትህ ቸር ነኝ
ሰውንም ለመርዳት ማንም አይቀድመኝ።
ጠጄ የሚጣፍጥ ዓለም ያወቀው
ጠላዬም እንዲሁ በጣም ዝነኛው
በጣና ዘልዬ በዓባይ ስቀዳው
ዓለሙን ያጠግባል ማለቂያም የለው ።
በቡሬ ምድጃ በዘጌ ጉልቻ
ቡናውም ይደርሳል ጥቂት ቈየኝ ብቻ ።
ከናውጋ ጎታዬ ጠመጁን አፍሼ
ከጐተራው ሞጣ አተሩን ቸርፍሼ ።
ከጉስጉሻው ሜጫ ግፊ ዳጉሳውን
አረቂን አውጥቼ ጠምቄ ጠላውን ።
ይገሮው እመጣለሁ ምንም ሳይጐድል
አትፍራ ወዳጄ አይዞህ ጸጥ በል ።

ልብ
ሰምቼ ነበረ ሰዎቹ ሲያሙሽ
ምንም ዘመድ ቢሞት አታዝንም ሲሉሽ
እያሉ አትላጭም መቼም ራስዋን
ደግሞም ትቀባለች ዘለዓለም ቅቤን ።

አሁን ግን ነገርሽኝ አንች በንደበትሽ
እንግዲህ አልሰማም ቢያማ ጠላትሽ ።

**ኢትዮጵያ** መቼም አላለቅስ ጠጕሬንም አልላጭ
እንደአረመኔ ሰው በጕልዳፋ ምላጭ ።
መቼም አላለቅስ ጥቅም በሌለው
የሞተ ላይመጣ ደግሞም ላይረባው ።
አዘንተኞችን ግን አጥናናቸዋለሁ
የሚያስፈልገውን የዝን እየሰጠሁ ።
መጽሐፍ ይላልና ካዘኑት እዘኑ
ከተደሰቱትም አብራችሁ ዝፈኑ
የእግዚአብሔር ወዳጆች ጻድቃን እንድትሆኑ ።

**ልብ** እባክሽ እማዬ ፍቀጂ ልጠይቅሽ
ማስተዛዘን እንጂ በሰፊው ደግሰሽ
ሙሾን እያወረድሽ በሰፊው ገጥመሽ
አታሞ እየመታሽ ግጥም ደርድረሽ
እልቅሶ ማቀንቀን በሰው ፊት ቁመሽ ።
አታውቅም ወይ ለካ እስከ ዛሬ ድረስ
በጣሙን ገረመኝ እንደምን ልታገስ ።

**ኢትዮጵያ** አሁንስ ተናገርህ ክብሬን የሚነካ
ከልቅሶዬ ሁሉ አታውቅም ወይ ለካ ! ።
ብዙ ግጥም አለኝ እኔስ በሀገሬ
እነአልቅሶ አይቀብር እነዘፍኖ አይድሬ
እንደምን አላችሁ የዳጉሳ አንጋሬ ።
በጣም አስደነቀኝ ያሁኑ ነገርህ
ዋናውን ሥራዬን አለማወቅህ
እልቅሶ ታወቂያለሽ አታውቂም ብለህ
እንዴት በሰው መኻል ትጠይቃለህ ።
አሁንም ጥራና ጓደኞችህን
አወርድልሃለሁ በሞላ ግጥሜን።
አንተ ካጠናኸው ሁኖልህ ተግተህ
ይህማ ምን ገዶ ሳለሁ እናትህ ።
እልቅሶዬ ቅኔ ደግሞም ጎብር ነው
በጣም ይጣፍጣል ለሚሰማው ሰው ።
አላለቅስም እንጂ መቼ አላውቅም አልሁ
በላ እንግዲህ ስማኝ ላወርደው ጀመርሁ ።

እልቅሰዬንና ደግሞም ሙሾዬን
ለማወቅ ከፈለግህ ጠልቀህ ምሥጢሩን
ማሻሻል አለብህ አማርኛህን ።
ሰምንና ወርቅን ኅብሩን ሳመጣብህ
ዐይንህ ሲጉረጠረጥ ይጨነቃል ልብህ ።
ውስጠ ወይራውና ደግሞም ምርምር
ሰም ለበስ ጉዳና ሌላውስ ይቅር ።
ሳትረዳው ቀርተህ ሳይገባህ ምሥጢሩ
እንደ ቀላል ነገር ሌሎቹ ሲያወሩ ።
ትላለህ በይፋ ለሚሰማህ ሰው
ግጥሙ ምንም አይደል ረብም የለው ።
አዬ ልጄ ልጄ ታሳዝናለህ
የሰው ስታጠና የራስህን ትተህ
በቀደም ባወራህ ድንግርግር አለህ ።

ል ብ — ያንችን ቅኔ መፍታት እኔን ቸግሮኝ
እስቲ ተናገሪ ልየው ሲጨንቀኝ ።

ኢትዮጵያ — አውጥተህ አውርደህ ደክመህ ለመረዳት
አትመኝም አንተ ሳለልህ ምክንያት ።
ትላለህ እየዞርህ ላገኘኸው ሁል
እንዲህ ያለስ ጣጣ በነጮችም የል ።
በቅኔ በአገባብ በሐሳበ ባሕር
እኔ እንደማልበልጠው ሌላውን ሀገር ።
የኔን ሳታጠና የናትህን ሙያ
ትነሆልላለህ ያላንዳች ገበያ ።
ቢገባህ ባይገባህ እኔ ምን ቸገረኝ
በል ስማ ልንገርህ አንተው ከጠየቅኸኝ
ትካዜ ሲይዘኝ አዘን ሲገባኝ
አንጐራጕለሁ እንዲህ እያልሁኝ ።

ብዙ ጊዜ ተነሳሕያን የሚሉት የበገናና የምርምር ቅኔ ።

ጊዜያቱ መሸብኝ ሳይ ሌላ ሳይ ሌላ
የተሰቀለውን ያን ሥጋ ሳልበላ ። (ኅብርና ምርምር)
ብትከሳ ብትጠቍር ብትሞት ምን አባቷ
ሥጋዬ ናትና የነፍሴ ጠላቷ ።
እኔስ ካገሬ ላይ ቤትም አልሠራሁ

በዳሞት መካከል ተቀምጫለሁ ።
በመለኮቱ ሲኖር
ለመላእክቱ ሲያስቸግር ።
ተነሣ እግዚአብሔር ለሰው
መዋረዱ እንጂ ነው ።
የወንጌል ቃል አንድ ይበቃል
አለመስጠት ያጸድቃል ።
የዛሬ ዘመን ጓደኛ
ምሥጢር አይነግሩት አብሮ አይተኛ ።
መተኛቱንስ ይተኛል ሽተት ብሎ ይገኛል ።
አንድ በሬ ቢኖር በበረቴ
አበያ ሆነ በሀብቴ ።
አላርስም አለ ብጠምደው
ተው አርጂ ልብላው ።
የጌታችንን ራት ምሳ
ዛንገዳና ዳጉሳ ።
እበላዋለሁ ይሙላ ጎኔ
መቼም ከፍ አልል እኔ ።
ከጐጃምና ከዳሞት
ማን ይበልጥ ይሆን በስፋት ።
እንዲያውም ባየው ብተቸው
ታላቁ ዳሞት ነው ።
ላስታ በጌምድር ትሁልደሬ
ቢሆን በወደድሁ አገሬ ።
ምን ዕዳው ነበር ቢቀር
ከዳሞት መፈጠር ።
ደንበጫ ስደርስ መሸብኝ
ገና ዳሞት አለብኝ ።

## ራስ አሊ ወደ ጐጃም በተሻገሩ ጊዜ ።

የጐጃምን ዶቄት ክርትፍ ነው እያሉ
ራስ አሊ መጡ አስልመው ሊበሉ ።

## የብሩ ጉሹ ።

እኛስ እንላለን እቴጌ መነን
አሊ ማን ይላታል ያችን እናቱን (አሊ.ማን) ።

ይመልሰው እንጂ እግዚአብሔር ባወቀ
ጣር ቅጠል አይቀርም ያስ ላም ዝለቀ ።
ጥቂት ሰው ሞተ አሉ ከጋሎች ከተማ
አያሌ አይሞትም ወይ ደስ እንዲለኝማ ።

## ደጃች ተድላ ሲሞቱ ።

የንጉሥ አሽከር ጠፍቶ ሲፈለግ ሌሊት
ቀን ከተድላ ጋራ ሲሄድ ዐየሁት ።
ሀገሬ ዳሞት ታሥሯል አሉ
ገንዘብ ጠፍቶበት ለሁሉ ።
ሰንሰለት ሲጮኽ ሰማሁኝ
ተፈታ መሰለኝ ።
ቄላ ወርጄ ጥጥ ብዘራ
አላብብ አለኝ አላፈራ ።
ምን እለብስ ብዬ ሲጨንቀኝ
አፈራለሁ አለኝ ።
ልጁን አባቱ ተጣልቶት
እረግሞት እረግሞት ።
ይታረቀዋል ደግሞም
እረግሞት አይቀርም ።
ቤተ ስኪያን ስሜ ስወጣ
ልብሴን ቀደደው ጋሬጣ ።
መርፌና ፈትል ይጃለሁ
ጠቃሚ ሰው አጣሁ ።
እተማሪ ቤት ልከውኝ
በዚያው መንገዱ ጠፍቶኝ ።
አልማር እንደሆን
በባል በሥራው አልባክን ።
የእግዜር ለምዱ እኔ ነኝ
በሥጋዬ ያለፉኝ ።
ተጣልቻለሁ ካምላክ ጋራ
በጥቂት ነገር ባንድ እንጀራ።
እሱ እንኳ አይበላ ሆድ የለው
እያደላ ለሰው ።

## ዐይቶ አጣ ።

መልካም አደራሽ ሠርቼ
መቃን መድረኩን አበጅቼ ።
አንድ ቀለም ሳጋ ጉድሎብኝ
ባጥ አከፋ አሉኝ ።
ባጥ አይከፉብኝ ምነው
ደገፋ የሌለኝ ሰው ።
ውዳሴ ማርያም ደግሜ
ተቀምጬ አደርሁ ደክሜ ።
በመቊጠሪያዬ ሳንቀላፋ
ዋ ! መቋሚያዬ ጠፋ ።
የሸንበቆ ቤት መሥራት
ተጠንቅቆ ነው በብልሃት ።
ዋ ! አለማወቅ ትልቅ ዕዳ
ሲቀልሰው ተጐዳ ።
ግድግዳውንስ የግዱ
ይችልልኛል ዘመዱ ።
ባጥ አያዳፉኝ ምነው
የጐረቤቴ ሰው ።
ቊምጥና የለ ከቤቴ
በእናቴም ሆነ ባባቴ ።
እንጀራ ቈርሶ ማን ባበላኝ
እኔማ ጣቴ አስጠላኝ ።
በጭንቅ አደርነ ባሳር ጠባ
ሰው በሰው እየገባ ።
አሻግሬ ባይ መንገዱን
እረ ሰው ምናምን ።
በእናቱ ነው እንጂ የሰው ልጅነቱ
ካብነቱ በቀር ምን አለው አባቱ ።
አብ ካልሰጠኝ ብዬ ምነው መናደዴ
ለወልድ አልነግርም ወይ ለሥጋ ዘመዴ ።
የሴት ወይዘሮ ስትሄድ
ምጥ ይዟት ነበር በመንገድ ።
መንፈስ ቅዱስም ነገረኝ

አባባት መሰለኝ ።
አላወቀችም ይሆንን
ወልድ አምላክ መሆኑን ።
ጣፍጦኝ እንዳልበላ ይምረረው ብለኸኝ
ምነው በሥጋ አሞት ደባልቀህ ሰጠኸኝ ።
እንኳን ደኅና ገባህ ከሄድኀበት አገር
ጠላቶችህ ሁሉ ይቅር ብለው ነበር ።
አላኰራኝ አለ ክንዴን ብንተራሰው
እንዴት አንድ መጠጊያ ከቤቱ ያጣል ሰው ።

## እልቅሶ ።

ዘመድ ሲሞትብኝ ኀዘን ሲገባኝ
እያቀነቀንሁኝ አለቅሳለሁኝ ።
አማርኛ አጣርተህ ለመስማት ከቻልህ
ከልቅሶዬ ደግሞ ስማኝ ልንገርህ ።

## ወንድሟ በሰው አገር ቀርቶ ።

የሰው አገር በሽተኛ
ካውራ መንገድ ላይ የተኛ ።
አትቀስቅሱት አልበቃል
አገርሽቶት ይሞታል ።

## ደጃች እንግዳ ኤልያስ የምሥራች የምትባል ልጃቸው ስትሞት ያለቀሱት ።

እንደ ወዲያ ሰዎች እንደ ወሰንተኛ
የምሥራች ሞተች የሚሉ አማርኛ ።
መሬት ገዛች እንጂ ጉልትን አስጐለተች
መች ተብሎ ያውቃል የምሥራች ሞተች ።
እኛም ብንናገር ሰውም ብንጠይቅ
የምሥራች ሞተች ተብሎም አያውቅ ።

## ነፍሰ ጡር ስለሞተች ።

ተዋት እባካችሁ የልቧን ታድርሰው
ቢይዟት ቢይዟት አትገላገል ሰው።
ተባል አያኖርም እንዲህ ያል ጠባይ

ቢይዙሽ ቢይዙሽ አትገላገይ ።
አራሲቱ ወተት ጠጭ ይሻልሻል
አልቦ ይዞ አባትሽ ያስፈርድብሻል ።

## ወንድሚ ከጦር ሜዳ የሞተባት ።

አሞራው ንገረኝ ከወደቀበቱ
ወዳጁም አንተ ነህ የበላህ ከፊቱ ።
እኔ አላይም እንጂ አንተስ ታየኛለህ
በአሞራ ላይ ሁነህ በደጄ ታልፋለህ ።
ዘማች ምንም ቢሆን ያዝንለት አያጣ (እናቱ)
አሞራ እንኳ ሂዶ ፊቱን ነጭቶት መጣ ።
ንገረኝ አሞራ እኔ ነኝ እናቱ
ባለሚል አንተ ነህ የበላህ ከፊቱ ።

## ስለ እናት ።

አንድ ላም አለችኝ ሆዴ ሚወዳት
እናት በቅሎ ባገኝ በለወጥሁባት ።
ከዚያ ማዶ ሁና ትጣራለች እናት
ናብላ ነው እንጂ ሌላም ጉዳይ የላት ።
እናት ሰፊ ሜዳ ከሜዳም ድልድል
ያን መርዘኛ ጠላት ራብ የምትገድል ።
ዕይዋት ከዚያ ማዶ ያች ቅጠል ምንድር ናት
አስተውሎ ላያት ወይን ናት ወይን ናት ።
እናት ዐውድማ ናት የተለቀለቀ
ብትሰጠው ብትሰጠው አትልም አለቀ ።

## የመርጠሽን ሁለት ልጆች አንድ
## የሚባል ወንዝ ስለበላባት ።

ሁለቱን አንድ ዘንድ ለምን ሰደድሻቸው
መርጠሽ ከልጆችሽ ባስቀረሽላቸው
ካንድ ሁለት ይሻላል ብዬ ብሰዳቸው
ኮርክ ላይ መጣልኝ የሁለቱም መርዷቸው ።

## እሼቱ የሚባል አጋሚዶ ስለተደበደበ ።

ቆለላ አይደለም ወይ እሼቱ አገርህ ?
ይልማና አይደለም ወይ እሼቱ አገርህ ?
የጁ ነው እያሉ የደበደቡህ ።

## አባ ገብረማርያም የሚባሉ ሰው እንደሞቱ እኅታቸው ስለተደገመች ።

የአባ ገብረማርያም ተሰቅሏል ዳዊቱ
አውርዳችሁ ስጧት ተደገመች እቱ ።

## የመርጌታ በቃ ምሽት ጐንጅ ።

ድጓውን ምዕራፉን አስተጋቡት በጣም
በቃ ተከተት እንዲግህ አይወጣም ።
ካህን ሞተ ብሎ አይነግሩም አዋጁ
እንዲያው በየደብሩ መልአከ ነበር እንጂ ።

## ደጃዝማች ተድላ በሞቱ ጊዜ ።

ውኃ ዋና እንኳ አላውቅ ዋ! ምን ይበጀኝ
ጌታ የውሽ ገቡ የዳ ጥለውኝ ።
የንጉሥ አሽከር ጠፍቶ ሲፈለግ ሌሊት
ቀን ከተድላ ጋራ ሲሄድ ዐየሁት ።
የውሽ ወስደው ጣሉት ደጃዝማች ተድላን
ይነሣ ነበረ አብማ ቢሆን ።
በጐንደር ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው ፤
በትግሬ ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው፤
በሸዋ ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው ፤
ተድላ ጓሉ ሙቶ ጐጃም ሊፈታ ነው ።
እሻ እሻ ነው እንጂ የመኰንን ሞት
እንዲያ አልቀሰው ተድላን ለምን ቀበሩት ።
አልሞተም ይላሉ ደጃዝማች ተድላን
አሁን እሑድ ሲቀር የምናውቀውን ።
ጌታው ደጃች ተድላ ወዴት ሂደው ቀሩ
ትላንት ወደ ማታ ገበያ ነበሩ ።
እሳት ፈጀው አሉ ጌታው ቤትዎን
ከገበያ በላይ የነበረውን ።

## ደጃች አመዴ ጐጃምን ሲገዙ ።

መስታዋት አልገዛ ወርቅ የለኝ ከቤቴ
በምኔ ልጥረገው አመዴን ከፊቴ ።

## የንጉሥ ተክለሃይማኖት ።

ከበር ሲመታ ቅኔ ሲዘመር
ጽናጽል ንጉሡ አያውቁም ነበር ።
በሰኔ በግንቦት የሰማሁት ወሬ
አላውራ ብዬ ነው አለመናገሬ ።
ምነው በቅዳሜው ምነው በሰንበቱ
በሥራ አይደለም ወይ ንጉሡ የሞቱ ።
ወይፈኑ ጊደሩ ተርፎለት ከሜዳ
ምን ከፉ ዘራፊ አውራ የሚነዳ ።

## በእየጊዜው ከተዘረፉት ከደራሲው ያማርኛ ቅኔዎች የሚከተሉትን እንጠቅሳለን ።

ደራሲው ባባቱ ሞት ጊዜ ያለቀሰው
አባቴን ንገሩት ርቆ ሳይሄድ
በጣም ሳይገሠግሥ በያዘው መንገድ ።
ምንድር ጉድ ነው ብዬ ቁሜ ሳመነታ
መጥፎ ወሬ ሰማሁ ትላንትና ማታ ።
ርዳት ብሎኝ ሄደ አሚኑን ጥሏት
መቼ እወዳታለሁ እናቴን ካባት ።
እወደው ነበረ ከልብ አባቴን
አሁን ግና ወደድሁ ከአባት እናቴን ።
ድንግል ነው ይላሉ ቀርበው ያላዩህ
አባት መባልህን ያላወቁብህ ።
ለካስ መጽሐፍ መማር ከንቱ ድካም ነው ፤
ለካስ ቅኔ ማወቅ ከንቱ ድካም ነው ፤
ለካስ ብዙ መማር ረብም የለው ፤
የሚሾቱን ቃል ኪዳን እሱ አፈረሰው ።
ሞገስ ብልህ ነበር በቀድሞ ዘመን
እናት ውደድ ብሎ ሲመክረኝ እኔን
እንግዲህ አላምንም ካባት እናቴን ።
ማስተማሩን ትቶ ያን ሁሉ ትምህርት
ጭቅነት ተሾመ በጣም ኰራባት ።
በሰው አገር ሁነህ መኰራትህ ለምነው
አንተ ጭቃ ብትሆን አፈሩ የኗ ነው ።

ጭቅነቱን ካንተ እስካገኝ ድረስ
መሬቱን ከእናቴ ደግሞም እስክ ወርስ
አባቴ አትቄጣ እባክህ ታገስ ።

## የደራሲው እናት የሞቱ ጊዜ ። ስማቸው ወርቀነሽ ነው ።

ብዙ ነገር ሳስብ ወርቅነሽ ቢሉኝ
መቼ ብረት ሁነሽ አፈር በላብኝ ።
ብዙ ገንዘብ ይዞ የማይገበዩሽ
ሁሉ የሚወድሽ እናት ወርቅነሽ ።
ሞገስ ከተለየኝ ወርቄንም ካጣሁ
መከራዬን እንጂ መቼ ዓለማየሁ ።
ባንገቴ ልሠርሽ በእጄ ልያዝሽ
ማጌጫ መዣሪያ እናት ወርቅነሽ ።
አባቴን ቀብሬ አንችን ሳስከትል
በጣም አፍራለሁኝ ዓለማየሁ ልል ።
በእየሰው ደጃፍ እንዳይረካከስ
እናት የልጅ ግርማ ወርቅ ነሽ ሞገስ ።
ሞገስ ጭቃ ሁኖ ከተሾመልሽ
ያፈሩን ግብር ከፋይ ጥሬ ወርቅነሽ ።
እንደምንም ብሎ ሊሠራ ነው ቤቴ
አፈሩን ከእናቴ ጭቃውን ካባቴ ።
ካገሬ ላይ መኖር በጣም አኰራኝ
በአባቴ ጭቃ ሹም በእናቴ አፈር ነኝ ።

## ተወዳጁ መስፍናችን ልዑል መኰንን ኀ. ሥ. የሞቱ ጊዜ ።

ያለም አሳላፊ ሞት እንዴት ከበረ
መኰንን መኰንን ይጠራ ጀመረ ።
መኰንን ሲጠራ መኰንን ሰማና
እየሮጠ ሄደ ፈጥኖ በመኪና ።
መስፍን ሀገረ ገዥ ይሆን የነበረ
ሀብቱ ተሰናክሎ ጭቃ ሁኖ ቀረ ።
ጭቅነት ተሹመህ ቤተ ክስያን ስትዞር
ግዛቱ ቀረልህ ተበተነ አገር ።
ጊዜው ብራ ነበር ያውም አልደመነ

እግረኛው ደኅና ሳል በእግሩ እየማሰነ
የሰማው ሰው ሁሉ ማንም አላመነ
በመኪና ሲሄድ እንዴት ጭቃ ሆነ
በመኪና ሲሄድ ልብሱ ጭቃ ሆነ ።
አፈር የለበሰ ሲሄድ በመኪና
መኰንን ምን ሆነ አይደለም ወይ ደኅና

የግሪክ ት. ቤት መምህራን የልዑልነታቸውን የሕይወት ግብር ባጭሩ የሚገልጥ ቅኔ ስለፈለጉ ከደራሲው የተሰጠ የማርኛ መዝሙርና ቅኔ ።

በትምህርት ጎዳና ብትመራው ሕዝቡን
ሕፃን ተከተለህ ደጉን መኰንን ። (አዝማች)
ሕዝባችን በሞላ አመሰገነህ
ጋብዘህ ብታጠግበው በሰፊው ግብርህ ።
ደኃው ደስ አለው መኰንን ባንተ ላይ
በደገኛው ግብርህ ስላገኝ ሲሳይ ።
በፀሐይ ብርሃን ግብርህ ቢታየው
በገና ችሮታን መኰንን ቃኘው
ሲሠራ ለዋለ በጣም ሲደክመው
ማረፊያው አንተ ነህ ለሕዝብ መጠጊያው ።
ሀገራችንን ለቆ ጠፋልን ስንፍና
መኰንን በግብርህ ተፈሪ ነህና ።
መኰንን አንተ ነህ ጋሻው ለጠቅል
ጦር የማይበግረው ቢመጣ በኀይል ።
የነጻነት ታጋይ ያገሬ ጠበቃ
መኰንን አንተነህ ለዓለም የምትበቃ ።
በትምህርት ጎዳና ብትመራው ሕዝቡን
ሕፃን ተከተለህ ደጉን መኰንን ።

የአፈወርቅ ገ. ኢየሱስን መጻሕፍ፤ ጦቢያውን አማርኛ የማያውቅ ሰው አርማለሁ ብሎ ስላበላሻት በጋዜጣ ከተጻፈው ባጭሩ ።

አንት ሰው መግፋቱን ጠልቼ
ባንድ ጐኔ ብቻ ተኝቼ ።
አድሬ ነበር ስቸገር

አሁንስ ባሰኝ ልናገር ።
ጦቢያው ልጃችን ባልገሽ
ከቋንቋ ክፍል ገብተሽ
በማያውቁት ቃል ለፍልፊሽ
ጨዋ እንድትሆኝ አረሙሽ ።
ምን አቀለበለበሽ ጥንቱን
መናገርሽ ከባዱን ።

ጦቢያው ትመልሳለች።

አፌን ዘግቼ በፍርሃት
ዝም እንዳልል ዘለለት
ይጠፉብኛል ቃላት ።
ይህንም ብዬ ብናገር
ቀጡኝ ቈረጡኝ በምር ።
ተቈርጬ ከመኖር
ይሻለኝ ነበር መቃብር።
ያልተማረ ጨዋ አጐት
ከቤቴ ስኖር በትምህርት
አንድ ቀን ጠርቶ ድንገት
ምንም ሳያምረኝ ሳያሰኘኝ
ያለጊዜዬ ተገደረኝ ።
ብዙ ጉድ አለ አባት ሲሞት
ልጅ ይሰደባል ያለጥፋት ።
ቋንቋው አይገባም ንግግሩ
ደግሞም መጥፎ ነው ምግባሩ ።
አባት ያለኝን በተናገርሁ
ተቀጣሁ ተኰረኰምሁ ።
ባልንጀሮቼ በጣም ፍሩ
እናንተንም አይለቅ ነገሩ ።
ብልግና መስሎት ምናገረው
እሱ ባያውቀው ባይረዳው ።
በጣም ነገሩ ቸገረኝ
ጨዋ ሁኚ ብሎ ቢቀጣኝ ።
ግዕዝ ካላወቀ አስተማሪ
አይበልጥም ለካ ከተማሪ ።

ስለዚህ ቃል ባይገባው
እውነቱን ሁሉ ሠረዘው ።

## ኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በገኘችበት ጊዜ ፤

የትላትናው ወዋ በጣም ሆነኝ ጤና
ሆድ ቍርጠቱም ጠፋ ግብጥ ምስር ቀርና ።
ድኅነት ከቀረ ከሆነ ሹም ሽር
እበላለሁ ሥጋ አልቀምስም ምስር ።

## ጃንሆይ ዓለም ስለጐበኙ ፤

ጀግናው አባ ጠቅል በተፈሪ ግርማ
ዓለምን መዞሩ ታወቀ ተሰማ
ካናዳ አሜሪካ ሜክሲኮ በሙሉ
አቋቋምህን ዐይተው ተፈሪ ነህ አሉ ።

## በፈተና ጊዜ የተቀኖቸው ።

ይኸ መምህራችን እንዴት በደለኝ
ሁሉንም ሠርቼ አንድም ሳይቀረኝ
የሥራዬን ዋጋ አንድ ዜሮ ሰጠኝ ።
ወዳያውም ብጠይቅ ነገሩን አክርሮ
በል ተቀመጥ አለኝ አንድ ዜሮ ጨምሮ
ደግሞም ተናገረ ወደ ልጆች ዞሮ
ሰንፎም ለሚተኛ ላጠናም ጠንክሮ
እሰጣቸዋለሁ ለሁሉም አንድ ዜሮ
ወዳያው ብንጠይቀው ሁላችን ባንድ አፍ
ምንድር ነው መለዮው ትጉና ሰነፍ
ተኝቶ የኖረ ያጠናም ሳያርፍ ።
አልበ ሚቀበሉ ሁለቱም ከሆነ
ታዲያስ ትጉሁ ልጅ በከንቱ ማሰነ ።
ወዳያው መለሰልን ነገሩን አዛውሮ
ከናንተ መካከል ቢያጠና ጠንክሮ
እኔ እሰጠዋልሁ አንድ ሁለት ዜሮ ።

## በአማርኛ ሰምና ወርቅ ፤ ኅብር ፈተና ጊዜ ።

ፈተና፤ ፈተና መሆኤን በጣም ረሥታችሁ
ትሰድቡኝ ጀመረ ቀላል ናት ብላችሁ ።

ሕፃናት አንድ ጊዜ ስሙኝ ልንገራችሁ
ለጨዋታ ብዬ ጥርሴን በሳያችሁ
ለሰዎች አታውሩ ቀላል ናት ብላችሁ ።

ተማሪ፤ ፈተና በሬ አይደል ወይም ነብርን
እኔም አይደለሁኝ ምጠብቅ ጥጃን
የት ያምጣው ብለው ነው መምህራችንን
ንገረኝ የሚሉኝ ካለበት ጎብሩን፤
የተማሪ ጣጣ መቸውንም አያልቅ
እረ እንዴት ይገርማል እንዴትስ ይደንቅ፤
ምግዛበት ሳጣ መጽሐፍና ጨርቅ ።
ገብር ብለው ያዙኝ ሰም ለመብራታቸው
ወርቅንም ለዋጋ ደግሞም ለጥቅማቸው ።
ሰምስ እሰጣለሁ እንደ ተቻለኝ
ወርቃቸው ነው እንጂ የሚያስቸግረኝ ።
ወይስ ቄስ አይደሉ ለጧፍ አይሆናቸው
ወይ ንጉሥ አይደሉ አልገብርላቸው ።
እረ በምን ስም ነው ይህን የጠየቁ
አምጣልኝ እያሉ ሰሙን ከነወርቁ ።

<u>ወገን በማጣት ምክንያት የጻፍናቸውን መጻሕፍት</u>

<u>ትምህርት ሚኒስቴር ካመሰገነ በኋላ ሳይገዛቸው</u>

<u>ስለቀረ የሚከተሉት ተጻፉ ።</u>

ዘመነ ማቴዎስ ይህ ዘመን
በጣም ጠሞኛል እኔን ።
ችግር ቢጠና ቢጨንቀኝ
የበላዮቼን ጠየቅሁኝ ።
ነገር ሳላበዛ ሳላትት
ሐሳቤን አቀረብሁ በጽሕፈት፤
የጠየቅሁትም በውነቱ
ግዙኝ ነበረ በከንቱ፤
እምቢ ብለው መለሱኝ
አማራ እንገዛም አሉኝ፤

ይህን ብሰማ እኔም
ነደደኝና በጣም
መለስሁላቸው ተቈጥቼ ።
ብዙውን ነገር አትቼ ፤
ደኅን ካልገዛችሁ ሲመጣ
የሰው ልጅ እከ ነጻ ወጣ ፤
እነሱም መለሱ አንድነት
የሚከተለውን በሥርዓት ።
የሰው ልጅ ብትሆን ኑሮ
እንገዛህ ነበር ዘንድሮ ።
ይህን ስላሉ ገርሞኝ
ወዲያውኑ ጠየቅሁኝ ።
እነሱም አረምን ብለው
ነገሩኝ ስልቱን አዛውረው ።
የሰው ልጅማ ብትሆን ኑሮ
ትገዛን ነበር ዘንድሮ ።
ሲዘባርቁ በማየቴ
ነደደኝና ካንጀቴ ።
ያየሁትን ታሪክ እኔም
ነገርኋቸው በግጥም ።
የሰውን ልጅ የሰው ልጅ
ይግዛው እጅ በእጅ ።
አይደለሁም ወይ ከሁለት አንዱ
እያለፉኝ የሚሄዱ ፤
ግዙኝ ስል የጠሉኝ
ልግዛ ስልማ ቢሰሙኝ ።
ሳይቈጡ አይቀርም በምር
እረ እንደምን ሁኜ ልኑር ፤
ግዙኝ ብል ከጠሉኝ
ልግዛ ብልም ከነሡኝ ።
እንግዲህ እኔ ምመርጠው
ባንዱ ተሸጠ መኖር ነው ።
ተሸጬም እንዳልኖር ባንዱ ደጅ
ዋጋ አጣ የሰው ልጅ ።